በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

ሆሣዕና
የዐቢይ ጾም ስምንተኛ ሳምንት

ሆሣዕና ከስምንቱ የዐቢይ ጾም እሑዶች አንዱና የመጨረሻው ሳምንት ሲሆን ከትንሣኤ ቀድሞ የሚገኝ የሕማማት መግቢያ ዋዜማ ነው። **ትርጉሙም እባክህ አሁን አድን ማለት ነው።** ይህ ቃል በዘመነ ብሉይ በቀደምት ነቢያት ዘንድ የተለመደ ቃል ነው። "አቤቱ እባክህ አሁን አድን፣ አቤቱ እባክህ አሁን አቅና፣ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።" እንዲል መዝ.117፥25-26

ምስባክ: በዕለቱ የሚሰበከው ምስባክ ይህ ነው፦

"ንፍሑ ቀርነ በዕለት ሠርቅ። በእምርት ዕለት በዓልነ። እስመ ሥርዓቱ ለእስራኤል ውእቱ" መዝ.፹፩÷፫-፬
ትርጉም፦ በመባቻ ቀን በታወቀችው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ፤ ለእስራኤል ሥርዓቱ ነውና÷ የያዕቆብም አምላክ ፍርድ ነውና። መዝ. 80፥ 3-4

ወይም

"እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሓተ። በእንተ ጸላዒ። ከመ ትንሥቶ ለጸላዒ ወለገፋዒ።" መዝ. ፰÷፪
ትርጉም፦ ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ። ስለ ጠላት÷ ጠላትንና ግፈኛን ታጠፋው ዘንድ። መዝ. 8÷2

ሆሣዕና አስቀድሞ ካለው ረቡዕ ጀምሮ የሚታሰብ ታላቅ የቤተክርስቲያን የበዓል ቀን እንደሆነ ይታወቃል። ይህን ስም በዚሁ ሰንበትና በዋዜማዎቹ ዕለታት የሚዘመረው ጾመ ድጓ 'ሆሣዕና በአርያም" 'ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት" 'ዕለተ ሆሣዕናሁ አርዓየ... ' ወዘተ. በማለት ይጠራዋል። ሆሣዕና የሚለውን ቃል ቅዱስ ያሬድና ሌሎችም አባቶች በየቦታው እየጠቀሱና እየተዘመረለት በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም የገባበትን ሁኔታ እየተረከ ስለሚዘምር ይህ ሰንበት በጌትነትና በክብር በውዳሴና ቅዳሴ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ በሽማግሌዎችና በሕፃናት አንደበት በድንጋዮችም ልሳን ሳይቀር እየተመሰገነ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በክብር ሲገባ ለሰጣቸው ለተቀደሰ ሰላሙና ፍቅሩ መታሰቢያ ሆኖ የተሰጠ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ቀን እንደ ተራ ሰው ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ይገባ ነበር።

በዚህ ቀን ግን የአይሁድ ንጉሥ ሆኖ በክብር ገባ። ከቢታንያ ተነሥቶ ደብረ ዘይት ሲደርስ ከሐዋርያቱ ሁለቱን በቤተፋጌ ሰው ተቀምጦባት የማያውቅ ውርንጭላ እንዲያመጡለት ላካቸው። "በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሒዱ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርሷ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም አምጡልኝ። ማንም አንዳች ቢላችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ" አላቸው። ማቴ. 21፥1-17 ወደ ቤተፋጌም ሄደው አህያይቱን አገኙአት። ሲፈቱአትም ሳለ ባለቤቶቹ መጡባቸውና አስቆሟቸው። እነርሱም ኢየሱስ እንደፈለጋት ነገሩአቸው። ባለቤቶቹ ይህንን ሲያውቁ ተዋቸው። ሐዋርያትም የአህያይቱን ውርንጭላ ፈትተው ወደ ኢየሱስ ወሰዱ። አጠገቡም ሲደርሱ ልብሳቸውን በአህያይቱ ውርንጭላ ላይ አንጥፈው ኢየሱስን አስቀመጡት።

በዚህም በነቢዩ ዘካርያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ። **"... እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።** " ዘካ.9፥9። ጌታችን በአህያ ጀርባ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ የሰላም ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል። እስራኤል ዘመነ ምሕረት ሲሆንላቸው አባቶቻቸው በአህያ ጀርባ ተቀምጠው ይታዩ ነበር። ጌታም እውነተኛ የኅሊና ሰላም ይዤላችሁ መጣሁ ሲለን በአህያ ጀርባ ወደ ቤተ መቅደስ ሕይወታችን ተጉዟል።

ለታሰሩት መፈታትን ሊሰብክ ሰው የሆነ ጌታችን ከማሰሪያዋ በተፈታች አህያ እንደተቀመጠ ሁሉ **ከኃጢአት እስራት በተፈታ ሕይወት ዛሬም ያድራል**፤ የኅሊና ሰላምን ይሰጣል። ስለዚህ **ንስሐ ገብተን ጌታችንን "ሆሳዕና በአርያም" እያልን ልናመሰግነው ይገባል።**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!
የቅዱስ ጳውሎስ ሕክምና ግቢ ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፴፣ ፳፻፲፭ ዓ.ም